**መጋቢት 25 2020**

# <u>የጭብጥ ወረቀት፡ COVID-19 መታያ ማዕከል / ማገገሚያ ማዕከል</u>

## መሠረታዊ መግለጫ

- ምልክት ለምታይባቸዉ ወይንም COVID ያለባቸዉ አዋቂ ሰዎች ለመለየት የህብረተሰብ ጤና መመሪያን መከተል ለማይችሉ፣ ለይቶ ለመቀመጥ፣ ወይንም በቤታቸዉ ለማገገም፣ ወይንም ቤት ስለሌላቸዉ በህብረተሰብ ጤና ተቆጣጣሪነት እንክብካቤ ለመስጠት የታቀደ ትልቅ የህብረት እንክብካቤ ተቋም።
- መታየ ማዕከልና ማገገምያ ማዕከል ተቋማት ለሆስፒታሎች እንደ አማራጭ ቦታ ልያገለግሉ ይችላሉ፤ በዚያም አሳሳቢ ያልሆኑ የCOVID ክስተቶችን ወደ መታየ ማዕከልና ማገገምያ ማዕከል አስወጥቶ የሆስፒታል አልጋዎችን በጣም አጣዳፊ ለሆኑ ክስተቶች ነጻ ማድረግ ይቻላል።
- በሠራተኞችና አቅርቦቶች እጥረት፣ ኪንግ ካዉንቲ በካዉንቲዉ ጠቅላላ ከብዙ ትንንሽ ቦታዎች ይልቅ በርካታ ትላልቅ ቦታዎችን ለማቋቋም እያሰበ ነዉ።

## ሐሳብ

- <u>ህዝብ:</u> መለየት፣ ለይቶ ማቆያ ዉስጥ መሆን፣ በራሳቸዉ ቤት ማገገም ለማይችሉ አዋቂ ሰዎች። ይህም ተጓዦችን፣ ምልክት የታየባቸዉ ወይንም ጤናቸዉ የተጎደ ወይንም ቤታቸዉ ያሉ ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው በCOVID የተያዙ ግለሰቦች (አረጋዉያን፣ በሽታን መከላከል አቅማቸዉ የደከመ፣ ህጻናት፣ የመሳሰሉት) ወይንም ቤት አልባ ሰዎችን ይጨምራል።
- <u>መጠን:</u> ይለያያል፣ ባንድ ቦታ እስከ 350 ሰዎች።
- <u>ሠራተኞች:</u> በቦታ እስከ 80 ሠራተኞች፤ የጤና ሠራተኞችና የጤና በለሙያዎች ያልሆኑትን ጨምሮ እንደ ማዕከሉ መጠን። እያንዳንዱ ቦታ ሁል ግዜ በቦታዉ ያለ ዳሬክተርና ሐኪም፣ ሦስት የደህንነት ሰዎች ዉስጥና ዉጪዉን የሚቆጣጠሩ ይኖሩታል። ምግቦች ለሁሉም እንግዶች ይቀርባል።
- <u>ትራንስፖርት:</u> ከማዕከሉና ወደ ማዕከሉ የትራንስፖርት አገልግሎት በጣም አግባብ በሆነ መንገድ ይቀርባል።
- <u>የእንክብካቤ ደረጃ</u>፡ በህብረተሰብ ጤና ተቆጣጣሪነት የሚሰጥ እንክብካቤ ምልክት ያለባቸዉንና በማገገምያ ዉስጥ ያሉ COVID ያለባቸዉን ይደግፋል። ይህም መሠረታዊ የነርስ አገልግሎት፣ ወሳኝ ምልክቶችን መቆጣጠር የመሳሰሉትን ይጨምራል። ኪንግ ካዉንቲ በ መታየ ማዕከልና ማገገምያ ማዕከል ማገገምን ከምያፋጥኑ መደበኛ እንክብካቤ ባለፈ ሌላ ህክምና ይኖራል ብሎ አይገምትም። ማንኛዉም ከፍ ያለ እንክብካቤ የምያስፈልገዉ ወይንም አስፈላጊ የሆነ ህክምና ማግኘት ያለበት ፈቃድ ወዳለዉ የህክምና ተቋም ይጓጓዛል።
- <u>ምርመራ/ህክምና:</u> መታየ ማዕከልና ማገገምያ ማዕከል የታቀዱት ይኖራል ተብሎ ለምታሰበዉ ብዙ ቁጥር ላላቸዉ የCOVID ምልክት ያላቸዉና COVID የያዛቸዉ ግለሰቦች ግዜያዊ ማገገምያ ቦታ መልስ ለመስጠት ነዉ። ከፍ ያለ ስጋት ያለባቸዉ ህዝቦችን ምርምራ ከመስጠት በተጨማሪ እያንዳንዱ ተቋም የምርመራ ዉጤቶችን ለሚጠብቁ ና ተመርምረው ለተገኘባቸዉ የተለየ መለያ ቦታዎችን ያቀርባል። ሁሉም የላቦራቶሪ ጥንተና ከቦታዉ ዉጪ ነዉ የምሠራዉ።